# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. መ ግ ቢ ያ ፤

የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ከኀዳር 29 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር እንዲሆን በአዋጅ ቁጥር 916/2008 ተደንግጓል፡፡

ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 25/1984 እና በደንብ ቁጥር 50/1991 መሠረት የህግ የሰውነት መብት ያለውና ራሱን የቻለ የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በአዋጁና በደንቡ ድርጅቱን የማስተዳደር ሥልጣን ተሰጥቷል፡፡ ከዚህም ሥልጣንና ተግባር መካከል የድርጅቱን ንብረት የማስተዳደር ኃላፊነት ነው፡፡

በዚሁ መሠረት የልማት ድርጅቶችን ስልጣንና ተግባር በሚወስነው አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት በድርጅቱ ህልውና ላይ ወሳኝነት የሌላቸውን ቋሚ ንብረቶች ሽያጭ በድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ፀድቆ የሚከናወን መሆኑን ስልጣን የሰጠ በመሆኑ ድርጅቱ አሁን ያለውን በድርጅቱ ህልውና ላይ ወሳኝነት የሌላቸው ከፍተኛ መጠን ያላቸው እና ቋሚ ያልሆኑ ንብረቶች በድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነታቸውን በመገምገም በሽያጭና በሌሎች የማስወገጃ ዘዴዎች ማስወገድ አስፈላጊ በመሆኑ እንዲሁም ከዚህ በፊት እየተሠራበት የነበረውን አሠራር የበለጠ ግልፅ ዘመናዊ ቀልጣፋና ውጤታማ የሚያደርግ የንብረት አወጋገድ ስርዓት ማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ ድርጅቱ ይህንን የንብረት አወጋገድ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. ዓ ላ ማ:-

ድርጅቱ ራዕዩን ከግብ ለማድረስና የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ሲሰራ ለድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በመስጠት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ያላቸው ሚና አኳያ ሲታይ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዘነ ሆኖ የሚታመንባቸውን ቋሚና ቋሚ ያልሆኑ ንብረቶች በማስወገድ ዘመናዊ ግልፅና ተጠያቂነት ያለው የንብረት አወጋገድ አሠራር ስርዓት እንዲኖር ማድረግ የዚህ መመያ ዓላማ ነው፡፡

## 3. የመመሪያው አስፈላጊነት፡-

የድርጅቱ የንብረት አያያዝና አወጋገድ ስርዓት በህግና አሠራር ስርዓት ግልፅና ዘመናዊ እንዲሁም ተጠያቂነት ከማስፈን አኳያ በየደረጃው ያለው አመራርና ሠርተኛ በንብረት ማስወገድ ስርዓት ኃላፊነቱን በብቃት እንዲወጣና ወጪ ቆጣቢ እና ቀልጣፋ የንብረት አወጋገድ ሥራ የሚሠራበት መመሪያ በማስፈለጉ ነው፡፡

## 4. ኃላፊነት፡-

የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የገበያ ልማት የደንበኞች አገልግሎትና ሽያጭ ሥራ አስፈፃሚ ይህ መመሪያ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 5. ስ ያ ሜ –

ጳህ መመሪጻ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ንብረት አወጋገድ መመሪጻ ቁጥር ___________ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 6. የተፈፃሚነት ወሰን፤

ይህ መመሪያ በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 7. ትርጉም፡-

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሐረጎች የሚከተሉት ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

1. “ቋሚ ንብረት” ማለት በንብረትነት ታውቆና ለብቻው ተለይቶ ለመመዝገብ የሚችል የተገዛበት ዋጋው ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) ያላነሰ እና ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ የጠቀሜታ እሴት የሚኖረው እና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ንብረት ነው፡፡
2. “አላቂ ንብረት” ማለት ከቋሚ ንብረት ውጪ የሆነ ማንኛውም ንብረት ሲሆን የገንዘብ መጠኑ ከአንድ ሺህ በታች ሆኖ ጥቅም ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ንብረት ነው፡፡
3. “ተረፈ ምርት” ማለት በደንበኛው ወይም በድርጅቱ የሥራ ትዕዛዝ መሠረት በምርት ማምረት ወይም በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ ወይም ከተጠናቀቀ በኋላ የምርት አካል ያልሆነ ለደንበኛው ወይም ለድርጅቱ በትዕዛዙ መሠረት ርክክብ የማይፈፀምበት ወይም ለሽያጭ ያልዋለ እና ተመልሶ ለምርት ግብዓትነት የማይውል የጥሬ ዕቃ ቁርጥራጭ፣ የምርት ቁርጥራጭ፣ እንዲሁም የተበላሸ ምርት፣ የወረቀት ኮር፣ እና አገልግሎት የሰጠ ፕሌት እና ሌሎች ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ንብረቶች ነው፡፡
4. “ኮንቴነር” ማለት ድርጅቱ ለሚገዛቸው ቋሚ ንብረቶችና ቋሚ ያልሆኑ ንብረቶች ወይም አገልግሎቶች ማሸጊያዎች ናቸው፡፡
5. "ተሽከርካሪ" ማለት በመንገድ ላይ በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ ወይም የሚጐተት ለሰው እና/ወይም ለዕቃ ማጓጓዣ የሚውል ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው፣
6. "የእርጅና ቅናሽ" ማለት ንብረቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይሰጣል ተብሎ በሚገመትበት ዕድሜ ስርዓት ባለው አኳኋን የንብረቱን ዋጋ እንደወጪ እያሰቡ መቀነስ ማለት ነው::

7. "ስቶክ" ማለት በድርጅቱ የተመረቱ ወይም የተገዙ ወይም በእርዳታ የተገኙ ንብረቶች ሆነው በመደበኛው የስራ እንቅስቃሴ ውስጥ አገልግሎት ላይ እስከሚውሉ ድረስ በመጋዘን የተቀመጡ ቋሚ ዕቃዎች፣ መሣሪያዎችና አላቂ ዕቃዎች ማለት ነው።
8. የሥራ አመራር ቦርድ ማለት የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ ነው፡
9. "ሚኒስቴር" ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው፡
10. ድርጅት ማለት የመንግሥት ልማት ድርጅት ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 25/1984 እና በደንብ ቁጥር 50/1991 መሠረት የሚተዳደር የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ነው፡
11. ንብረት ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ ሰባት ንዑስ ቁጥር 1,2,3,5 የሚገኙ ማንኛውም ዕቃዎችን ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት

# የንብረት አወጋገድ፣

## 8. ንብረትን የማስወገድ ስልጣን፡-

ድርጅቱ በዚህ መመሪያ መሠረት ንብረቶችን የማስወገድ ሥልጣን አለው፡፡

## 9. ንብረት እንዲወገድ የመፍቀድ ስልጣን፡-

1. ከድርጅቱ ቋሚ ንብረት እንዲወገድ የመፍቀድ ስልጣን የተሰጠው ለድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ነው፡፡

2. ቋሚ ንብረት ያልሆኑ ንብረቶችን እንዲወገዱ የመፍቀድ ስልጣን የተሰጠው ለድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ነው፡፡

## 10. የድርጅቱ ንብረት የሚወገድበት ምክንያቶች፡-

ድርጅቱ በሚከተሉት ምክንያቶች ንብረትን ማስወገድ ይችላል::

ሀ. ንብረቱ ለድርጅቱ ዓላማዎች የማይፈለጉ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ. ንብረቱን ይዞ መቀጠል የሚያስከትለውን ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ የማያዋጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ. በልዩ ልዩ ምክንያት ንብረቱ የሚፈለግበትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በብቃት መስጠት የማይችል ወይም ከአገልግሎት ውጪ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

መ. ድርጅቱ ከሚኖረው የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ ዕቅድ አንጻር ትርፍ መሆኑ ሲታመን፣

ሠ. ንብረቱ ለምርት አገልግሎት ተመልሶ መስጠት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ

ረ. ንብረቱ መጠገን የማይቻልበት ሁኔታ መኖሩ ሲረጋገጥ፣

ሰ. ንብረቱ ለጤናና ለአካባቢ ብክለት አደገኛ መሆኑ በሚመለከታቸው አካላት ሲረጋገጥ፣

## 11. ንብረት የማስወገድ ሂደትና ኃላፊነት፣

1. ንብረቶችን በባለቤትነት የመከታተልና የመጠቀም ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል የሚወገዱ ንብረት ዝርዝር በቃለ ጉባዔ አስደግፎ ለድርጅቱ በላይ ኃላፊ በወቅቱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2. "የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በቃለ ጉባዔ ተደግፎ የቀረበለትን የሚወገዱ ንብረቶች ተመልክቶ ለዝርዝር ግምገማ ለንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ ይመራል፡፡"

3. የድርጅቱ ንብረቶች አስወጋጅ ኮሚቴ የተመራለትን ንብረቶች ዝርዝር ግምገማ በማድረግ የውሳኔ ሀሳብ ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

4. የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በአስወጋጅ ኰሚቴ የቀረበለትን ውሳኔ ሀሳብ መርምሮ በአንቀፅ 9(1) መሠረት ቋሚ ንብረቶች በሥራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ከተፈቀደ በኃላ ለአስወጋጅ ኰሚቴ ይመራል፡፡ ቋሚ ያልሆኑ ንብረቶችን በአንቀፅ 9(2) በማፅደቅ ለንብረት አስወጋጅ ኰሚቴ ይመራል፡፡

5. የሚወገዱ ንብረቶች ልዩ ጠቀሜታ ያላቸው ወይም በማስወገድ ሂደት ጉዳት የሚያስከትሉ ስለመሆናቸው አግባብ ካላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ጋር መነጋገር ይገባል፡፡ የሚወገዱት ንብረቶች በባህሪያቸው ለጤና አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎች ወይም መድኃኒቶች ወይም የጨረር ጉዳት የሚያስከትሉ ስለመሆናቸው እና ስለአወጋገዱ አስፈላጊውን እገዛ ከሚመለከታቸው አካል ትብብር መጠየቅ አለባቸው፡፡

## 12. የሚወገደውን ንብረት የመነሻ ዋጋ መገመት፡-

1. ድርጅቱ የመዝገብ ዋጋ ለሌላቸው ቋሚ ንብረቶችና እንዲሁም ዋጋ ያላቸው ማሽነሪዎች፣ ተሽከርካሪዎና ህንፃዎች የሽያጭ መነሻ ዋጋ የሚገምት ገማች ኮሚቴ በዋና ሥራ አስፈፃሚ መቋቋም ይኖርበታል፡፡

2. የዋጋ ገማች ኮሚቴ አወቃቀር ስልጣንና ተግባር፡-

የዋጋ ገማች ኮሚቴ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ የሚቋቋም ሲሆን የሚከተለው ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

ሀ. እንዲወገድ የተወሰነበትን ንብረት የመነሻ ዋ ገምቶ ለድርጅቱ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

ለ. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች ሙያው ያላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የመነሻ ዋጋውን አገማመት በተመለከተ እንዲያማክሩት ሊጠይቅ ይችላል::

ሐ. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጠየቀው የሙያ ምክር ከንብረቱ ልዩ ባህሪ የተነሣ የንብረቶቹን አጠቃቀም በተመለከተ ስልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸውን የመንግሥት ተቋማት ወይም በዚህ ሙያ የተሠማሩ የግል ድርጅቶችን ወይም ግለሰቦችን መሆን ይኖርበታል::

መ. የመነሻ ዋጋን የገመተ ኮሚቴ በአወጋገድ ሥራው መሳተፍ የለበትም::

## 13. ንብረት የማስወገጃ ዘዴዎች ፡-

ሀ. ለሌላ የመንግሥት መስሪያ ቤት በማዛወር ወይም በማስተላለፍ፣

ለ. ባለበት ሁኔታ በግልፅ ወይም በውስን ጨረታ ወይም በሐራፅ በመሸጥ ፣

ሐ. ንብረቱን ፈትቶ በመለዋወጫነት ጥቅም ላይ በማዋል ወይም በመሸጥ ፣

መ. ንብረቱን በውዳቂነት ማስወገድ፣

ሠ. ንብረቱን በመቅበር ወይም በማቃጠል ማስወገድ::

ረ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በርሜሎች፣ የቀለምና የኬሚካል ኮንቴነሮች፣ ቁርጥራጭ እንጨቶች እና ሌሎች ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ዕቃዎች በድርጅቱ ማኔጅመንት ውሳኔ ለሠራተኞች ዋጋ ገምቶ ሊሸጥ ይችላል፡፡

## 14. ንብረትን ለሌላ የመንግሥት መስሪያ ቤት በማስተላለፍ ለማስወገድ፣

በመንግሥት መስሪያ ቤቶች መካከል የሚደረገው የንብረት ዝውውር የሚፈጸመው የወቅቱን የንብረቱን ዋጋ ግምት በመመዝገብ መሆን አለበት::

## 15. ንብረቱን ባለበት ሁኔታ በግልፅ ጨረታ፣ ወይም በሐራጅ መሸጥ፡-

1. ንብረት በግልፅ በውስን ጨረታ ወይም በሐራጅ ለመሸጥ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች፣

ሀ. የድርጅቱን ንብረትን በጨረታ ወይም በሐራጅ በመሸጥ ማስወገድ ይቻላል::

ለ. ድርጅቱ የተሻለ ዋጋ ለማግኘት፣ በፍጥነት ሽያጩን በመፈፀምና የሚያስከትሉትን ችግሮች በመገምገም የተሻለውን □መሸ□ □ጸ መምረዓ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም በግልፅ ወይም በሀራጅ ሊሸጡ ይቻላል፡፡

ሐ. የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ ለጨረታ ወይም ለሐራጅ የሚቀርቡትን ዕቃዎች የመነሻ ዋጋ በድርጅቱ □በላጁ ኃላኝ መጽደቃቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

መ. ተ□ትተዉ □እንዲሸጡ የተወሰነባቸውን መለዋወጫዎች፣ □ፊ ረታ□ ወይም የሐራጅ መነሻ ዋጋ የመለዋወጫውን የገበያውን ሁኔታና ሌሎች መረጃዎችን መሠረት በማትረ□ የተገመተ መሆን አለበት::

## 16. በፊ ረታ ስለሚ□ረ□ ሽጸ□ ፡-

ሀ. የተጫራቾች የጨረታ ሰነድ ዝርዝር ሁኔታ በንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ የሚወሰን ሆኖ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ መጽደቅ አለበት::

ለ. ድርጅቱ በፊ ረታ□ ማስታወቂጸዉ □እስከተመለከተው ጊዜ ድረስ ክፍት ሆኖ የሚቆይ □ተለ□ □ፊ ረታታሣጥን ማዘጋጀት አለበት:: አስወጋጅ ኮሚቴውም □ፊ ረታ ሣጥኑን ማሸግ አለበት:: ማናቸውም ለጨረታዉ ማቅረቢያ የተሰጠው ቋ□ ካለ□ በኂላ □ሚቀርቡ የፊ ረታ□ ሰነዶች ሳይከፈቱ ለተጫራቾቹ መመለስ አለባቸው:: በጨረታ ሽያጭ በቂ ተወዳዳሪ ካልቀረበ ወይም የቀረበው ዋጋ ተቀባይነት ካላገኘ ድርጅቱ የጨረታውን ማስታወቂያ በድጋሚ የማውጣት ወይም ጨረታውን በመሠረዝ ሌላ የማስወገጃ አማራጭ የመጠቀም መብት አለው::

ሐ. ድርጅቱ ተጫራቾች የጨረታታ ማስከበሪያ እእንዲያስይዙ መጠየቅ ያለበት ሲሆን፣ ለእያንዳንዱ በጨረታታመከናወን ላለበት ሽያጭ የጨረታታማስከበሪያው መጠን በንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ መወሰን አለበት:: አስወጋጅ ኮሚቴውም ለእያንዳንዱ ሽያጭ የሚያዘውን የጨረታታማስከበሪያ በጨረታው ያሸነፈው ተጫራች እንደተመረጠና ውል እንደተፈፀመ ፊ ረታውን ላላሸነፉ ተጫራቾች መመለስ አለበት::

መ. ፊ ረታው ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸው እና አስወጋጅ ኮሚቴ አባላት ባሉበት ግልጽ ሆኖ መከፈት አለበት:: የተጫራቾች ስምና የመጫረቻዉ ዋጋ በኮሚቴ አስተባባሪ መነበብ አለበት፣ የሽያጭ ኮሚቴ ፀሐፊም ይህንኑ መዝግቦ መያዝ አለበት::

ሠ. ኮሚቴው የትኛውን የጨረታ□መዉፏ□ሪጸ ሀሳብ መቀበል □እንዳለበት ይወስናል:: ከፍተኛዉ ፊ ረታታበመነሻነት በተያዘው □ፉ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ኮሚቴው ከፍተኛውን የጨረታ□ □ፉ ሊቀበል ይችላል::

ረ. ኮሚቴው በጨረታው የደረሰበትን የውሳኔ ሃሣብ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ እንዲያፀድቀው ማቅረብ አለበት::

## 17. በሐራፀ ስለሚ□ረ□ ሽጸ□ :-

ሀ. ድርጅቱ □ሚጸወጣው □ሐራፀ ማስታወቂጸ ድርጅቱ ባዘጋጀው ቅጽ መሠረት ተሞልቶ መቅረብ አለበት::

ለ. የሐራጁ መሪ ሐራጁ ከመጀመሩ በፊት የመነሻውን ዋጋ መግለጽ አለበት:: በሐራጁ የመነሻው ዋጋ ወይም ከዚህ በላይ ንብረቱን የሚገዛ ካልተኛ □ንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ የተሻለ ነው የሚለውን የማስወገጃ ዘዴ መምረጥ አለበት::

## 18. የተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች ማስወገጃ መመዘኛዎችና ስለማስወገድ፣

የድርጅቱ ተሽከርካሪዎችንና መሣሪያዎችን ለማስወገድ ከሚከተሉት መመዘኛዎች ቢያንስ አንዱ መሟላቱን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

ሀ. በከፍተኛ ቴክኒካል ችግር ምክንያት ሊጠገን የማይችል ሲሆን፣

ለ. □መለ□ወ□ ክቃ በገበያ ላይ አለመገኘት፣

ሐ. ለማደስ የሚያስፈልገው ወጪ ከመተኪያ ዋጋው ጋር ሲነጻጸር መተካቱ የሚመረጥ ሲሆን፣

መ. በቴክኖሎጂ ኋላቀርነት ምክንያት ምርታማነቱ ዝቅተኛ ሲሆን፣

ሠ. ድርጅቱ ከሚኖረው ወቅታዊም ሆነ የቅርብ ጊዜ የሥራ ዕቅድ አንጻር ትርፍ መሆኑ ሲታመን፣

ረ. አገልግሎት በሰጠባቸው ጊዜያት ለጥገና የወጣው ጠቅላላ ወጪ ከሰጠው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ ሳይሆን ሲቀር፣

ሰ. በእርጅና ምክንያት አገልግሎት መስጠት የማይችል ሲሆን፣

ሸ. ተሽከርካሪው ወይም መሣሪያው የሚሠራ ከሆነ፣

ቀ. ተሽከርካሪው ወይም መሣሪያው የማይሠራ ቢሆንም ሞተር፣ ትራንስሚሽን፣ ሻንሲ፣ አካሉ እና ሃይድሮሊክ ሲስተም በሙሉ ያሉ ከሆነ፣

## 19. ቋሚ ንብረቶችን በጨረታ ሽያጭ ለማስወገድ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

ሀ. በሽያጭ የሚወገደው ንብረት ተሽከርካሪ ከሆነ ጨረታው ከመውጣቱ በፊት የባለቤትነት ማስረጃ መኖሩንና የቦሎ ግብር የተከፈለ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

ለ የጨረታ ሰነዶችን በማዘጋጀት ጨረታ ማውጣት፣ ማጫረት፣ ጨረታውን መገምገምና ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሪፖርት ማቅረብ፣

ሐ. የሽያጭ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ እና ንብረቱን ማስረከብ፣

መ. ተሽከርካሪን በሚመለከት የስም ዝውውሩ ለአሸናፊው እንዲፈጸም ለትራንስፖርት ባለሥልጣን ማስታወቅ::

ሠ. ንብረቱ በንብረትነት የተገኘበትን የሚገልጽ መረጃ ማጣራት፣

## 20. የተሽከርካሪዎች የመሣሪያዎች እና የሌሎች ቋሚ ንብረቶች □ፌ ረታ መነሻ ዋጋ

ሀ. መሣሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች በዚህ መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ ሲደረግ የመነሻ ዋጋ አተማመን በመንግስት መመሪያ መሠረት የጨረታ መነሻ ዋጋ ተወስኖ በጨረታ እንዲወገዱ ይደረጋል::

ለ. ሌሎች ንብረቶችን በጨረታ ዋጋ መሠረት ይወገዳሉ፣

## 21. ንብረቱን ፈትቶ በመለዋወጫነት ጥቅም ላይ ማዋል ወይም መሸዓ፣

1. ድርጅቱ የአንድን ንብረት አካላት ፈትቶ በመለዋወጫ ዕቃነት መጠቀም ወይም መሸጥ የሚችለው ንብረቱን ባለበት ሁኔታታመሸጥ የማይቻል ሲሆን ወይም ባለበት ሁኔታ□ ከመሸጥ ይልቅ ፈትቶ መጠቀም ወይም መሸጥ የበለጠ ጥቅም የሚያስገኝ ሲሆን ነው::
2. በመለዋወጫነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም እንዲሸጡ ከተወሰነባቸው ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች ላይ ጠቃሚ አካሎችን ፈትቶ አግባብ ባለው የዕቃ አስተዳደር አሠራር መሠረት ገቢ □እንዲሆኑና ጥቅም ላይ □እንዲውሉ ወይም በፌ ረታ□እንዲሸጡ ማድረግ ይቻላል::
3. ተ□ትተው፡ □እንዲሸጡ የተወሰነባቸው መለዋወጫዎች የጨረታታ መነሻ ዋጋ የመለዋወጫውን ዓይነት፣ የገበያውን ሁኔታና ሌሎች መረጃዎች መሠረት በማድረግ ማ ሞት ይኖርባቸዋል፡ ፡

4. ንብረትን ፈትቶ በመለዋወጫ ዕቃነት በሚሸጥበት ጊዜ የተፈታው ዕቃ ብረታ ብረት የሆነ እንደሆነ የሽያጩ ሂደት በመንግስት መመሪያ መሠረት መፈፀም ይኖርበታል፡፡

## 22. ንብረቱን በውዳቂነት ስለማስወገድ

1. ንብረት አስወጋጅ ኮሚቴው የተሻለ ስለሚሆነው ዘዴና ማናቸውንም ከውዳቂው ሊገኝ የሚችለውን የሽያጭ ገቢ በሚመለከት ምክር ይሰጣል፡፡ በውዳቂነት እንዲወገዱ የሚወሰኑ ሁሉ በድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ መጽደቅ አለባቸው፡፡

2. በውጭ እንዲወገዱ የተወሰነባቸውን ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች እንዲሁም ተፈትተው ጠቃሚ አካሎቻቸው የተወሰዱባቸው ቀሪ ብረታታ ብረቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም በፊ ረታ እንቲሸጡ ጁረፋል፡፡

3. ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር በመሆን ሥነ ምህዳርን በማይጐዳ ሁኔታ ውዳቂ ንብረቶችን በማቃጠልና በመቅበር ማስወገድ ይቻላል፡፡

## 23. ንብረቱን በመቅበር ወይም በማቃጠል ማስወገድ፣

ምንም ጠቀሜታ የሌላቸው ውዳቂ ንብረቶችን ድርጅቱ በራሱ ወይም የሚመለከታቸው አካላትን በማማከር በመቅበር ወይም በማቃጠል ወይም በሌላ መንገድ ማስወገድ አለበት፡፡ አፈፃፀሙ ሲከናወን፣

1. የሚወገደው ንብረት ምንም ዓይነት የስነምህዳር ወይም የጤና ችግር የማያስከትል ከሆነ ድርጅቱ በራሱ ኃላፊነት ንብረቶቹን ለይቶ በመቅበር ወይም በማቃጠል ማስወገድ ይችላል፡፡
2. የሚወገደው ንብረት ከፍተኛ የሥነምህዳር ወይም የጤና ችግር የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ድርጅቱ ስለአወጋገዱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ንብረቱን በተገቢው መንገድ ማስወገድ ይኖርበታል፡፡

# 24. የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ አወቃቀር፣ ተግባርና ኃላፊነት

በዚህ መመሪያ መሠረት የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ እንደሚከተለው ተዋቅሯል፡-

## 1. አወቃቀርና የስብሰባ ሥርዓት

### ሀ. የኮሚቴ አወቃቀር

የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ይቋቋማል፡፡ የሚቋቋመው ኮሚቴ ንብረቱን የሚጠቀምበት የሥራ ክፍል ያካተተ ሆኖ ብዛቱና ስብጥሩ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ወሰናል፡፡ የኮሚቴው የሥራ ዘመን ለሁለት ዓመት ሆኖ ለቀጣይ ሁለት ዓመታት እንዲሰሩ በድጋሚ ሊመደቡ ይችላሉ፡፡

### ለ. የኮሚቴው የስብሰባ ስነስርዓት፣

1. በኮሚቴው ስብሰባ ላጁ ሰብሳቢዉን ጨምሮ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
2. □ኮሚቴው ውሣኔ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፡፡ የኮሚቴው ትም□ □እኩል ሲሆን ኮሚቴው ሰብሳቢ ያለበት ወገን ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

## 2. የኮሚቴውተግባርና □ኃላፊነት፡-

ሀ. እንዲወገዱ ለተጠየቁ የድርጅቱ ንብረቶች የሚያስፈልጉ የማስወገጃ መጠይቆች፣ መረጃዎችና ሠነዶች ተሟልተው□እንዲቀርቡ ያደርጋል፣ ጸረፉ□□ል፣

ለ. እንቲዉ□ ጥያቄ የቀረበባቸው ንብረቶች ባሉበት ቦታ□በመገኘት ለውሣኔ የሚረዱ ግምገማዎችን ያደርጋል፡፡

ሐ በዚህ መመሪያ በተገለፁት የማስወገጃ መመዘኛዎችና የማስወገጃ ዘዴዎችንና ሰነዶችን መሠረት በማድረግ የሚወገዱ ንብረቶችን አወጋገድ ይገመግማል፣

መ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከሀ-ሐ በተገለጹት ግምገማዎች ላይ በመመሥረት □ውሣኔ ሃሳብ ለድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጸቀርባል፡፡

ሠ. እንዲሸጡ ውሣኔ የተሰጠባቸውን የድርጅቱ ንብረቶች የጨረታ መነሻ ዋጋ ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል በጨረታ ሰነድ ላይ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡

ረ. "የጨረታ ሰነድ በሚመለከተው የሥራ ክፍሎች እንዲዘጋጅ ያደርጋል"

ሰ. ማስታወቂያ ያወጣል፣ ጨረታ ይከፍታል፣ ያጫርታል፣ የጨረታውንም ውጤት ሪፖርት ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

## 25. ከቀረጥ ነጻ ስለሚገቡ ዕቃዎች፣

ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ለሌላ ወገን በሚተላለፉበት ጊዜ ስለ ቀረጡ አከፋፈል ሁኔታ የጉምሩክ አዋጅን ለማስፈፀም በሚወጡ አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

# ክፍል ሶስት
# ልዩ ልዩ

## 26. የበላይነት ያላቸው ህጐችና መመሪያዎች

በፌዴራል መንግሥት የሚወጡ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች ለዚህ መመሪያ የበላይነት ይኖራቸዋል፡፡

## 27. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሥራ አመራር ቦርድ ከፀደቀበት ከ............ ቀን ............... ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::